# ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው መንግስትና በሱማሌ መሃል ስላንዣበበው የጦርነት አደጋ ከትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ የተሰጠ መግለጫ

ህዳር 18 ቀን 1999 አም

የትብብር ለአንድነትና ዴሞክራሲ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ግንቦት 27 ቀን 1998 አም ባወጣው መግለጫ ሱማሌ ውስጥ አሳሳቢ ሁኔታዎች እየተከሰቱ መሆኑን አስጠንቅቆ፣ በተለይም በኢትዮጵያ ያለው የወያኔ/ኢህአዴግ አናሳ አገዛዝ፣ በሱማሌ ውስጥ ያለውን አሳዛኝ ሁኔታ ተጠቅሞ ራሱን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያገኝበት አስከፊና በየዕለቱም የሚያሽቆለቁል ሁኔታ ለማምለጥና፣ በህዝብ ዘንድ ያጣውን ተአማኒነትም ለመለወጥና ከፀረ ሽብርተኝነት ጎራ ተቀላቅሎ የአሜሪካን ዕርዳታ ለማግኘት ሊጠቀምበት እንደሚያሴር ፍርሃታችንን ይፋ አድርገን ነበር ። በስድስት ወራት ውስጥ ፍርሃታችን ዕውን ሆኗል ።

በዛሬው ዕለት እጅግ አስደንጋጭ ዜና ሰምተናል ። ይሄውም፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በሱማሌ ላይ የተጣለውን የጦር መሣሪያ እገዳ የሚያስነሳ ረቂቅ ሃሳብ ለተባበሩት መንግስታት የፀጥታ ጉባኤ የሚያቀርብ መሆኑ ነው ። ይህ እርምጃ መለስ ዜናዊ በሱማሌ ለሚያካሂደው ወሽቤ ፖሊሲ ህጋዊ ሽፋን ይሰጠዋል የሚል ፍርሃት አለን ። ትብብሩ፣ ይህ የአሜሪካ እርምጃ የአፍሪካ ቀንድ ተብሎ የሚታወቀውን አካባቢ ባጠቃላይ ጦርነት ውስጥ የመክተት አደጋ ያዘለ ነው የሚለውን «የአለምአቀፍ ቀውስ ቡድን» ግንዛቤ ሙሉ በሙሉ ይጋራል ።

በአለም አቀፍ ደረጃ በዋናዎቹ ሐይማኖቶች መሃል ውጥረት በተጠናከረበት ባሁኑ ሰአት፣ የሙስሊሙ አለም በምዕራባውያን ላይ ከፍተኛ ጥርጣሬ ባሳደረበት ቅፅበት፣ የኢትዮጵያ አምባገነን ሱማሌ ውስጥ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት በማድረግ፣ አደጋ ውስጥ የከረመውን የአፍሪካ ቀንድ ወደባሰ ቀውስ ለማዝቀጥ እየተጣጣረ ነው ። ይህም አድራጎት ካርቱም ላይ የተጀመረውንና ሱማሌን የማረጋገት አቅም ያለውን የሰላም አማራጭ የሚያጨናግፍ ነው ። የአለም አቀፉ ማህበረሰብ፣ የኢትዮጵያ አምባገነን ድሃይቱን ሃገር የማትሸከመው የጦርነት አበሳ ውስጥ የሚከትና፣ የከባቢያዊ ጦርነት አደጋ እንዲጠናከር የሚያግዝ ፍቃድ በመስጠት በሱማሌ ውስጥ ባለው ምስቅልቅል ሁኔታ ላይ ቤንዚን በማርከፍከፍ ማባባስ የለበትም እንላለን ።

የኢራቅ ሁኔታ እየተወሳሰበ በመሄድ የአዲስ ስትራተጂ አስፈላጊነትን ባስገደደበት ባሁኑ ወቅት፣ በዩ ኤስ በቅርቡ የተካሄደው ህዝባዊ ምርጫ ድምፅ የነፈገውን ፖሊሲ ዩናይትድ ስቴትስ መልሶ ሶማሊያ ላይ መጠቀም አይገባውም ። የዩ ኤስ አስተዳደር በአፍሪካ ቀንድ ላለው ቅምጡ ህጋዊ ሽፋን በመስጠት ለመጫር የሚጥረው ጦርነት ካካባቢውም አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ እንዳይሆን እንፈራለን ። በዚህ በተመሳቀለ ከባቢያችን ላይ የሚደረገው የሚዲያ ሥራና የዜና አዘጋገብ፣ በቅድመ ኢራቅ ጦርነት ወቅት ይካሄድ የነበረውን አይነት ሆን ተብሎ የሚነዛ የተሳሳተ መረጃ ያዘለ መሆኑ በመሬት ላይ ያለውን ሃቅ የማያንፀባርቅና አጣሞ የሚያቀርብ መሆኑ እጅግ አሳስቦናል ።

ትብብሩ፣ የአሜሪካ አስተዳደር፣ ሊያቀርብ ያሰበውን የጦር መሣሪያ ዕገዳ ማንሳት ረቂቅ በጥሞና እንዲመረምርና፣ ይልቁንም ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሱማሌ ወገኖች ያለማንም የውጪ ጣልቃ ገብነት ወደ ሰላምና ዕርቅ ፊታቸውን እንዲመልሱ ጥረቱን እንዲያጠናክር ጥሪ እናደርጋለን ። የኢትዮጵያ መንግስትም የቀረበለትን ሁሉን አቀፍ የሠላም ጉባኤ የመፍትሄ ሃሳብ ተቀብሎ ተግባራዊ በማድረግ፣ ሃገሪቱን ወጥረው ከያዟት ችግሮች ማላቀቂያ መንገድ እንዲፈልግና፣ ጎረቤት ሃገርን ከመውረር እንዲቆጠብ ተፅእኖ እንዲያደርግ ለአለም አቀፍ ማህበረሰብ ጥሪ እናደርጋለን ።

በሱማሌ ያሉ ወገኖች ሁሉ ከሁሉም አይነት አክራሪነት ተቆጥበው፣ ለድርድር፣ ለሚዛናዊነትና የጋራ ጥቅም እንዲቆሙ እየመከርን፣ ኢህአዴግና ተጠቃሚዎቹ ከባቢውን ወደማያባራ በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ የእርስ በርስ እልቂት ከሚከት መሰሪነት እንዲቆጠቡ እናስጠነቅቃለን ።

ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ